የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 31
ADDIS ABABA 4th March 2013

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፹፪/፳፻፭ ዓ.ም.
የሥራ ፈቃድ እና የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......ገፅ ፮ሺ፰፻፵፭

## CONTENTS

Regulation No. 282/2013

**Work Permit and Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulation ..........Page 6845**

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፪/፳፻፭

## የሥራ ፈቃድ እና የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያዎች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ ፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፻፸፬(፬) እና በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ አንቀጽ ፯(፩)(መ) እና አንቀጽ ፵፩ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሥራ ፈቃድ እና የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፪/፳፻፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "የሥራ ፈቃድ" ማለት አንድ የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመሥራት እንዲችል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፻፸፬ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 282/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF WORK PERMIT AND PRIVATE EMPLOYMENT AGENCY LICENSE FEES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2010, Article 174(4) of the Labour Proclamation No. 377/2003 and Article 7(1)(d) and Article 41 of the Employment Exchange Services Proclamation No. 632/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Work Permit and Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulation No. 282/2013".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "work permit" means a permit issued to a foreign national pursuant to Article 174 of the Labour Proclamation No. 377/2003 to work in Ethiopia as an employee;

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2:30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፪/ "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ" እና "ፈቃድ" በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤

፫/ ''ሚኒስቴር'' ማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤

፬/ "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፭/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፮/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል ::

## ፫. የሥራ ፈቃድ ክፍያ

ሚኒስቴሩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፩፻፸፬ መሠረት ለውጭ አገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ ሲሰጥ እንደሚከተለው የፈቃድ ክፍያ ያስከፍላል:-

፩/ የሥራ ፈቃድ ለመስጠት ..........ብር ፩ሺ፯፻፤

፪/ የሥራ ፈቃድ ለማደስ .............ብር ፩ሺ፫፻፤

፫/ የሥራ ፈቃድ ለመተካት ............ብር ፩ሺ::

## ፬. የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያ

፩/ ሚኒስቴሩ በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፪) መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ እንደሚከተለው የፈቃድ ክፍያ ያስከፍላል:-

ሀ) ፈቃድ ለመስጠት..................ብር ፫ሺ፤

ለ) ፈቃድ ለማደስ ....................ብር ፪ሺ፤

ሐ) ፈቃድ ለመተካት ..............ብር ፪ሺ፭፻::

፪/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ እንደሚከተለው የፈቃድ ክፍያ ያስከፍላል:-

ሀ) ፈቃድ ለመስጠት...................ብር ፮፻፤

ለ) ፈቃድ ለማደስ.......................ብር ፭፻፤

ሐ) ፈቃድ ለመተካት ..................ብር ፬፻::

2/ "private employment agency" and "license" shall have the meanings assigned to them under sub-article (1) and (2) of Article 2 of the Employment Exchange Services Proclamation No. 632/2009;

3/ "Ministry" means the Ministry of Labour and Social Affairs;

4/ "competent authority" means the authority responsible for the implementation of the labour laws in Addis Ababa or Dire Dawa city administration;

5/ "person" means any natural or juridical person;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Work Permit Fees

The Ministry shall, in connection with work permit to be issued to a foreigner pursuant to Article 174 of the Labour Proclamation No. 377/2003, charge work permit fees as follows:

1/ for issuance of work permit…… Birr 1,700.00;

2/ for renewal of work permit ……Birr 1,300.00;

3/ for replacement of work permit...Birr 1,000.00.

## 4. Private Employment Agency License Fees

1/ The Ministry shall, in connection with private employment agency license issued pursuant to Article 5(2) of the Employment Exchange Services Proclamation No. 632/2009, charge license fees as follows:

a) for issuance of license.........Birr 3,000.00;

b) for renewal of license……..Birr 2,000.00;

c) for replacement of license...Birr 2,500.00.

2/ The competent authority shall, in connection with private employment agency license issued pursuant to Article 5(1) of the Employment Exchange Services Proclamation No. 632/2009, charge license fees as follows:

a) for issuance of license ……... Birr 600.00;

b) for renewal of license ….…. Birr 500.00;

c) for replacement of license…..Birr 400.00.

## ፭. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል:-

፩/ የሥራ ፈቃድ አገልግሎት ዋጋ ደንብ ቁጥር ፶፩/፲፱፻፸፱ (በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፮/፪ሺ፩ እንደተሻሻለ)፤

፪/ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፺::

## ፮. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል::

አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር



## 5. <u>Repealed Regulations</u>

The following regulations are hereby repealed:

1/ the Work Permit Fees Regulation No. 51/1977 (as amended by the Council of Ministers Regulation No.166/2009);

2/ the Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulation No. 34/1998.

## 6. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 4th day of March, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**